# ከተዘጋ ውሸታሙ ኢትቪ ይዘጋ ተድላ ጌትነት

## ጀርመን

አርብ የካቲት 14ቀን 2006ዓ/ም በተላለፈው የ ኢትዮጵያ ህዝብ አይንና ጆሮ የሆነው ኢሳት እዲዘጋ ወያኔወች ፈረንሳይ ለሚገኘው የሳተላይት ድርጅት መጠየቃቸውን አሰምቶናል በዜናው ደንግጫለሁ አሁንስ የወያኔ መንግስት አበዛው በ ኢትዮጵያውስጥ በርካታ የዜና ማሰራጫ መስሪያ ቤቶች አሉት የቁጥር መብዛት ሳይሆን የሚያስፈልገው ጥራት ነው ለመጥቀስ ያህል ኢትቪ ፤ፋና፤ኤፍኤም፤ኢትዮጵያሬድዮ፤ስማቸው ያማረ አሉት ግን ዘወትር ውሸት የሚደሰኮርባቸው አንድም ቀን እውነት ተላልፎባቸው አያውቅም  የ ኢትዮጵያ ህዝብ ምንም አይነት ወቅታዊ መረጃ በማያገኘበት ወቅት አንድለናቱ የሆነና ያለን ቢኖር መቸ ስአቱ ደርሶልን እያልን በጉጉት የምንጠብቀው እንደ አይናችን ብሌን የምንሳሳለት የ ኢትዮጵይውያን አይንና ጆሮ የሆነውን አንዲዘጋ አምባገነኖቹ ወያኔወች መጠየቃቸው እጅግ ያሳዝናል ከማሳዘንም አልፎ ኢትዮጵያውያንን የሚያናድድ ድፍረት የተሞላበት ድርጊት ነው ለነገሩ እኮ በወያኔወች ከተደፈርን ቆየን

ከተዘጋ ይልቅ ኢሳት ሳይሆን ምንም የማይጠቅመውና መስማት የማይችለው የውሸት መፈልፈያው የሆኑትን በሀገር ቤት ያሉትን የዜና ማሰራጫወች እንጂ **ኢሳትን** አይደለም

እኔ ለ ኢትዮጵያ ህዝብ እንኳን ደስአያለን እላለሁ ምክንያቱም በ አንድ ኢሳትሬድዮና ቴሌቭዝን ጣቢያ ወያኔ ይህን ያህል ከተንቦቀቦቀ ተጠንክረን 1ና2 ተጨማሪ ቢከፈት እኮ ወያኔ በፕሮፖጋንዳ የሚፈርስ ድርጅት መሆኑን እያሳየ ያለ ነው ለዚህም መድህኒቱ በ ኢትዮጵያውያን እጅ ነው እሱም መስማት ብቻ ሳይሆን ኢሳት ከዚህ በበለጠ ተጠንክሮ እዲቀጥል ማድረግ የ እኛ በስደት የምንገኚ ኢትዮጵያውያን ነን ይህ መልእክት የስርአቱን ደጋፊወችንም ይጨምራል ለምን የምትሰሙት ሌላ እውነተኛ ዜና ስለማታገኙ መደጎም አለባችሁ

ወያኔ ባሁኑ ጊዜ መያዣ መጨበጫ ያጣ አቅማዳው የተቀደደ ያህል ነው እየተንጠባጠቡ ነው ያሉት የሚያደርገውን አጣ አሁን ደግሞ በ ኢሳትና ባንዳንድ ታዋቂ ግለሰቦች ጋዜጠኞች የግል ፋይል ላይ የኮሚፒዩተር ቫይረስ መላክ ጀምሮል ግን ኢሳት ከወያኔ ቀድሞ በምሁራን የተደራጀ በመሆኑ ከ4ኪሎ ከወያኔ የሚተኮሰውን የቫይረስ ሚሳኤል ከሀገሩ ሰይወጣ በጸረቫይረስ እስከድሚሳኤል እዲመታ ተደርጎ እዛው መከላከያ ሚኒስቴርና አካባቢው ፍንጥርታሪው በካድሬወች ሶፍትዌር ላይ እዲወድቅ ተደርጎል

ባሁኑ ጊዜ ወያኔወች ካወቁበት ከ ኢሳት ብዙ ጥሩ ጥሩ ሞያወችን መቅሰም ይችላሉ ደግሞም እያስተማራቸው ነው ኢሳት ለማንም አይወግንም አያዳላም የሚወግነው የተቋቋመው ለሚጨቆኑ ለሚፈናቀሉ ለሚታሰሩት ለሚገደሉት ንጹሀን ዜጎች ድምጽ የሚሰማበት እንጂ የማንም አይደለም የግል ነው ከተባሉ ኢትቪ፤ፋና፤ኤፍኤም፤ኢ/ሬድዮ፤ያማራክልል፤የደቡብ ክልል፤ የ ኦሮሚያ ክልል፤የትግራይ ክልል፤የ አፋር ክልል፤የሱማሌ ክልል፤የ አዲስአበባ ክልል ጣቢያወች የ አንድን ድርጅት ድምጽ ብቻ የሚዘምሩት  ተቃዋሚወች በምንም መልኩ ለ ኢትዮጵያ ህዝብ በደላቸውን ሀሳባቸው የማይገልጹበት በመንገድ ሲያልፉ ካልሆነና ቀና ብለው ማየት የማይፈቀድበት ጣቢያ እንጂ ኢሳትን አይመለከትም ከገለልተኚነቱ የተነሳ የወያኔ ባለስልጣናትን ደውሎ መረጃ ሲጠይቅ ገና ከ ኢሳት ነው ሲባሉ ይንቀጠቀጣሉ ለቀረበላቸውም ጥያቄ መልስ አይሰጡም ግን ሁሉም ማታ ወደዱም ጠሉም ቤታቸውን ዘግተው ያደምጡታል በዘገባውም ይረካሉ ታዲያ በ11 ጣቢያወች እውነት ሳይነገር ቀርቶ በ እኛው የ3 አመት ታዳጊው በ ኢሳት እውነቱ ሲገለጥ ምን አስደነገጣቸው ኢሳት የሚዘግበው እጅግ ጥቂቱን ነው እንጂ የወያኔን ጉድ ተዘግቦ አያልቅም ሰለዚህ 11ዱ ውሸታሞች በ1ዱ ኢሳት ተሸንፈዋል በቀጣይም ይሸነፋሉ

ወያኔ የሚለው ቢያጣ ኢሳት የግንቦት 7 ነው ይላል አይደለም እንጂ ከሆነም እሰየው ይህም የሚያሳየው ወያኔ ግንቦት 7 አብዝቶ ይፈራዋል ማለት ነው እውነት ያስፈራል ግንቦት 7 የ እራሱ ድምጽ አለው ኢሳት ግን አሁንም በድጋሚ የማንም አይደለም የጭቁን ህዝቦች የብሶት ድምጽ ለ ኢትዮጵያውያን ያለ አድላዊነት የሚያስተላልፍ ነው ኢሳት የተቋቋመው በዜጎች ነው እንደ ኢትቪ በመንገስት አይደጎምም ኢሳት አይዋሽም መረጃ ቆርጦ አይቀጥልም የሀይማኖት የብሔር ልዩነት አያደርግም የሚመራው በካድሬ ሳይሆን በምሁራን ነው ኢሳት አሁንም በርታ አይናችን ድምጻችን ነው አይዘጋም ከ1 በላይ

ያድጋል ይመነደጋል ኢሳት የ እኔ ነው ከተዘጋ የውሸት መፈልፈያው ኢትቪ ይዘጋ ጥርቅም ብሎ ይዘጋ አይጠቅምም በመጨረሻም ኢሳት የ ኢትዩጵያውያን የግል ንብረት ነው የ እኔ ነው አሁንም የ እኔ ነው እንበላቸው